የጎንደር ሕብረት

gonderhibrert72@gmail.com /website: www.gonderhibret.org

07/04/18

# ማህሉ ድንበር ሳይሆን፤ ድንበራችን ይከበር!

ክብሯንና ነፃነቷን ጠብቃ ዘመናትን የተሻገራችው አገራችን፤ የነፃነት ታሪኳ ሲመዘዝ ጫፍ ላይ የምናገኘው ዕውነት፤ ማሰልጠኛ መአከል ገብተው ወታደራዊ ሳይንስ ቀሥመው ወይም ስንቅና ትጥቅ ከመንግሥት ተሰፍሮላቸው የቆርቆሮ ሰርዲን እየፈለቀቀላቸው በሙብላት፤ ውሃም በቦቴ እየቀረበለት በመጎንጨት በጥቅሉ የገዥዎቹን ተስፋ ስንቀው በሰሩት ገድል ላይ የተመሰረተች አገር አይደለችም።

ይልቁንም ጎስቋላ ኑሮን ከሚጋቱ ዜጎቿ አብራክ የተወለዱ ቆራጥ ልጆቿ በአንድም በሌላም ከታሪካዊ የኢትዮጵያ ጠላቶቿ ለመታደግ ደም አፍሰው አጥንት ከስከሰው አሁን የምንመካባትን አገር ያገኘናትን ዋጋዋ እጅግ ከባድ የሆነች አገር እንጂ!! በተቃራኒው ደግሞ ከታሪካዊ ባዕዳን ጠላቶቻችን ጋር በመወገን ህሊናቸውን ሸጠው በወገኖቻቸው ላይ ታሪክ ይቅር የማይለውን የክህደት ተግባር የፈፀሙ ጉድፍቻ ዜጎች እንዳሉን የተለያዩ የታሪክ መዝክሮች በሰሌዳቸው አስፍረዋል።

በተለይ ደግሞ ታሪካችን የጎደፈው፤ ክብራችን የተደፈረው ዙሪያ ከለላየን ጠባቂ ብላ፤ ዳሯ ላይ በርስት ጉልትነት ባስቀመጠቻቸው የሰሜኑ ተወላጆቿ ነው። ዛሬም እኒሁ የጉድፍቻ ልጆቿ ካለፈው ታሪክ ሳይፀጸቱ ስብዕናቸውን በመሸጥ ጥንት አያቶቻቸው ለጣልያን ያስደፈሯትን ቅድስት አገር፤ ዛሬ ደግሞ ለሱዳን ሊሥማሟት ላይ ታች ሲሉ ፊርማው የተቀደደባቸውን በደም ሊያቀልሙ ከባዕዳን የሱዳን ሰራዊት ጋር በመወገን፤ የጎንደርን መሬት ሳያስቡት ላመለጣቸው የሥልጣን መበቀያ ሊያደርጉብን ጦርነት ከፍተውብናል።

በእርግጥም ሱዳኖች ዓመቱን አስልተው ወገኖቻችን ማረስ ወይም ያረሱትን መሰብሰብ በሚጀምሩበት ወቅት የተለፉበትን መና ለማስቀረትና ለወደፊትም ላለማረስ ተስፋ እንዲቆርጥ አስልተውና ተመክረው የሚመጡት በራሳቸው ጭንቅላት አልነበረ፤ ገዳሪፍ/ ሱዳን ላይ ከትመው መላ ሱዳንን የሚቆጣጠሩትን የወያኔ ካድሬዎችን የተንኮል ምክር መሰረት አድርገው እንጂ። የአሁኑ ግን ልዩ ነው! ከእጃቸው እንደ እንቁላል ላይነሳ የወደቀውን ሥልጣናቸውን በበቃኝ ለማገባደድ ለመበቀል የመዘዙት ካርድ በአሶሣ፤ በወልቂጤ፤ በአዋሳም አልሰራም። የመጨረሻ ቂም መበቀያቸው ለማድረግ የፈለጉት ግን፤ ትግራይ መወለዳቸውን ሳይፀየፍ ተቀብሎ በማሳደግ ምኒሊክ ቤተ መንግሥት እንደሸኛቸው ሁሉ እ. ኢ. አ በ2008 ዓ. ም. ምሶ የቀበራቸውን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ደወል ያሰማውን የጀግናውን ጎንደር ሕዝብ ነው።

ይዞን ሊሞት እየተጠራሞተ ያለው በተቀደደ ጆንያ የተጀቦነው የወያኔው ቡድን በሁለት መንገዶች ጎንደርን ብሎም ኢትዮጵያን ሊበቀል ተዘጋጅቷል፤

1. ሳያስበው ያመለጠውን ሥልጣን መልሶ እጁ እንደማያስገባ በመረዳቱ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" እንዳለችው አህያ ኢትዮጵያን መግዛት ባለመቻሉ በሚችለው መጠን ዘር ተኮር ጦርነት ከፍቶ ኢትዮጵያንን እርስ በርስ አብላልቶ እየመጣ ያለውን ለውጥ ማክሸፍ፤
2. የዘረኞች መዳኀኒት ሆኖ፤ ፍርኃትን ሰብሮ፤ የተረገጥችዋን የነፃነት ባንዲራ ከፍ አድርጎ በማውለብለብ ለመላ ኢትዮጵያ የአንድነት ፈር የቀደድውን የጎንደር ሕዝብ የጠላትን ጦር ሸፋን በማድረግ ማጥቃትና ማስጠቃት ማለትም የሚችለውን ያክል ተጉዞ ንብረትና ህይወት አጥፍቶ መጥፋትን ነው።

ይህም ሰሞኑን ጊዚያዊ እርካታን አስገኝቶላቸዋል።

- ከሃያ ቀናቶች በፊት በጎንደር ጭልጋ አውራጃ፤ በመተማ ወረዳ ነፋስ ገብያ ቁ.1 ላይ ወደ ሃያ የሚቃረቡ ወገኖቻችንን ከሁለት በጭቃ ተጉዘው የተለያዩ የእርሻ ቁሳቁሶችን የሚያቀብሉ ሞተሮችን ጨምሮ ማርኮ ወስዷል።
- በዚሁ በጭልጋ አውራጃ/ መተማ ወረዳ ደለሎ ቁ. 4 አካባቢ የሚያርሱና የሚያሳርሱ ተተኪ የሌላቸውን ብዛት ያላቸው ታዋቂ ወገኖቻችንን ለአካባቢውም አራዓያ የሆኑ ወገኖቻችንን ገድለዋል ብዛት ያላቸው ወገኖቻችንን አቁስለዋል ንብረትም አቃጥለዋል። በመሆኑም የወያኔ ግፍና ጭካኔ ሲበዛብን፤ የለውጡ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይቅርታችንም ካልባቸው ቁጭታችን መራር! ጥንካሪያችን ኃይል ሆኗል!!

በመሆኑም የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት የተመሰረተበት አንዱና ዋንኛው ምክንያት እኒሁ ትግራይ በቀል ወያኔዎች የረዥም ጊዜ እቅዳቸው አድርገው የተነሱትን የኢትዪጵያ መሰረት የሆነችውን ጎንደርን የማጥፋት ተንኮል በዘላቂነት ለመዋጋት የግንባር ሰለባ የሆነውን የጎንደርን ሕዝብ ለዘለዓለም ድርጅታዊ ቅርጽ አስይዞ አጠናክሮ በማስቆም ከወያኔም ህልፈት በኋላም ቢሆን ሲመች በልማት፤ ፈተና ሲገጥመው ደግሞ የጠረፍ አጥር በማድረግ ጠንካራ የኢትዮጵያ ክ/ሀገር እንድትሆን በመመኘት ነው።

ይሁን እንጂ ለዚህ ቅዱስ ዓላማችን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ከመሰሪውና አጥፍቶ ጠፊው የቀን ጅብ የወያኔው መንጋ ባልተናነሰ መልኩ የጥፋት አደጋ መስለው ከፊታችን የተጋረጡትን አደጋዎች ሳንጠቁም አናልፍም። ዘረኝነት ከካንሰር ጋር በእኩል መልኩ የሚፈራና በቀላሉ የማይነቀል መርዝ መሆኑን እናምናለን። በኢትዮጵያችን ደግሞ በወያኔ ነርሶች እንክብካቤ በመላ አገራችን ለሃያ ሰባት ዓመት ሲሰጥ የቆየው ክትባት በቀላሉ የሚነቀል ሆኖ አላገኘነውም። ይህ በአሁኑ ሰዓት በዶ/ር አብይ መሪነት እየገፋን ያለነውን የዲሞክራሲ ጎዳና ጭምር እጅግ አደጋ ላይ የጣለ መሰናክል ጭምር ነው።

እውነትን ይዘን እንድንጓዝ ካሰብን፤ በጎንድርም ይሁን በአጠቃላይ የዳር ድምበር ጥቃት ሲያጋጥመን የመጀመሪያ ተጠቂዎች በአካባቢ የሰፈሩ የአንድ ወይም የሁለት ጎሳዎች ይሁኑ እንጂ፤ የተጠቃችው ግን ከወረድን ያችው ወረዳ ወይም ክ/ሀገር፤ ከፍ ስንል ግን እንደ አገር ኢትዮጵያ፤ እንደ ሕዝብ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ነን። ይህ ሆኖ እያለ በጎንድር የሱዳን ድንበር የደረሰብንን አደጋ ግንባር ቀደም ተፋላሚ የሆኑት አንሰው እንደ ጎንደሬ፤ ከፍ ብለው እንደ ኢትዮጵያውያን መሞግሥ ሲገባቸው የአንድ አማራ ጀግኖች ተፋላሚ ተደርጎ በየሚዲያው መራገቡ ጉልበታችን የሚያዝል፤ ወኒያችንን ውሃ የሚቸልስ ደካማ ከወያኔ የማይሻል የአገር ደባ ሆኖ እየታየ ነው።

በዘር የምንደራጀው፤ በዘር ሊያጠቃን የሚመጣን ጠላት ለመመከት ብቻ ነው!! ያን ቅዱስ መከላከል ደግሞ የግድ ከሚጠቃው ዘር መወለድን ብቻ አይጠይቅም፤ ሰው መሆንን ብቻ እንጂ። አገራችን ኢትዮጵያን የሚያጠቃ ትልቅ ጠላት ሲመጣብን ግን በዘር አዙሪት ውስጥ የምንዋዥቅ ከሆነ፤ ለማያጠቃን ደካማ ጠላት የጥቃትን በር እንደከፍትን መረዳት ይኖርብናል።

በመሆኑም፤ የመጀመሪያ ጥቃትን ለመከላከል እንደ ጎንደሬ በጋራ መቆም! ዘላቂ ጠላትን እንደ ኢትዮጵያውያን ማበር፤ መተባበር የቆየ ታሪካችን ቀጣይም ተወራራሽ ወኒያችን ይሁን እንጂ ለጊዜያው ፖለቲካ ፍጆታ የዘለዓለም ጥቃትን አንጋብዝ!!

በመጨረሻም፤ ድንበራችን ተደርፍሮ፤ ማህላችን ዳር ሳይሆን! አሁን በዶ/ር አብይ አህመድ እየተመራ ያለው የለውጥ አካል ለመላ አገራችን ዳር ድንበር ቋሚ የዋስትና ውል ከአጎራባች አገሮች ጋር እስኪያስር ድረስ፤ የገብያ ግርግሩን ተጠቅመው ጥቃት ከሚያደርሱ እኩይ ጎረቤቶቹ የሚታደግ ወይም የሚያግዝ ጠንካራ የመከላከያ ሰራዊት በድንበር አካባቢ እንዲያሰፍር የጎንደር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት ያሳስባል።

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

የጎንደር ሕብረት

gonderhibrert72@gmail.com /website: www.gonderhibret.org

ጎንድር ሕብረት ለኢትዮጵያ አንድነት።